# የፌዴራል ስርዓቱ ተቻችሎ መኖርን እያጠናከረ ነው

**ዘላለም በቀለ 09-18-14**

ከመሰንበቻው በፀረ-ሰላም ሃይሎች አቀጣጣይነት የተከሰተውን ሁከት አስመልክቶ አንዳንድ ጨለምተኞችና የተቃውሞው ጎራ ባለሚሎች ችግሩ ሀገራችን በምትከተለው ፌዴራላዊ ስርዓት ሳቢያ የተከሰተ በማስመሰል አስተያየቶችን ሲሰጡ ይስተዋላል። በዚህም ስርዓቱ የችግሮች ምንች የሆነ ያህል ነባራዊ ዕውነታውን አጣምመው ለማቅረብ እየሞከሩ ነው።

ዳሩ ግን ይህ እሳቤያቸው "ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ" እንዲሉት ዓይነት መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም ይህ የተሳሳተ ምልከታ የሚመነጨው ፌዴራላዊ ስርዓቱን ካለማወቅ አሊያም ሆን ብሎ ላለማወቅ ከመፈለግ የሚነሳ ስለሆነ ነው።

እንደሚታወቀው ፊውዳላዊና አምባገነናዊ ገዥዎችን ተጠቃሚ ያደረጉት ያለፉት ሥርዓቶች ሀገራችንን በሁለንተናዊ መልኩ ጎድተዋታል፡፡ ምጣኔ ሀብቷን አድቅቀዋል፤ ዜጎቿን ለችጋርና ስደት ዳርገዋታል፡፡ ይህ የታሪካችን አንድ አካል መሆኑ ጨርሶ አይካድም፡፡

በተለይ የጥቂት መኮንኖች ስብስብ የነበረው ወታደራዊው አምባገነናዊ የደርግ ሥርዓት የህዝቡን የትግል ውጤት በመቀማት ይልቁንም እንደ መልካም የ"ሥልጣን ዱላ ቅብብሎሽ" አጋጣሚውን በመጠቀምና ድሉን ወደራሱ በመቀልበስ በሀገሪቱ ላይ ተጨማሪ ጣጣ አምጥቶ ማለፉ የትናንት ትውስታችን ነው፡፡

ይህም ሆኖ ሕዝቦቿ ከደርግ ውድቀት በኋላ የተረጋጋች እና ዜጎቿም ተፈቃቅደውና አንድ የጋራ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መስርተው እርስ በርስ እየተከባበሩ በፈጠሩት ፌዴራላዊ ሥርዓት የፈጣንና ተከታታይ ልማት ተቋዳሽ የሚሆኑበት አገር ባለቤት ለመሆን በቅተዋል፡፡

ይህ እየጎለበተ የመጣውና የዴሞክራሲ ባህል እየተገነባባት ያለች ሀገርን ለመመስረት እልህ አስጨራሽ ትግልንና የህይወት መስዋዕትነትን ጠይቋል፡፡ ይህ በታሪክ ሁሌም የሚወሳ ሀቅ ነው፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ በምትከተለው ፌዴራላዊ ሥርዓት አያሌ ድሎችን ማስመዝገብ ችላለች፡፡ ሕዝቦቿም የውጤቶቹ ተቋዳሽ ለመሆን በቅተዋል፡፡ ይሁንና የቀድሞው ሥርዓት ተመልሶ ይመጣ ዘንድ ጨለምተኞቹ ሠላሙን አግኝቶ ኑሮውን ለመለወጥ የሚጣጣረውን ዜጋ ወደ ኋላ ለመጎተት የማይቀበጣጥሩት የለም፡፡

አስተማማኝነቱን በተግባር በማረጋገጥ ላይ የሚገኘውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በማጥቆር ሥራ የተጠመዱት እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን እድገትና አንድነት ሠላም ነስቷቸው የማይወረውሩት የአሉባልታ ድንጋይ የለም። ‘ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ለብተና የሚዳርግ ነው እያሉ ማጥላላትና ማጠልሸት ምን ትርፍ ያስገኝ፣ የትስ ያደርስ ይሆን?’

እንደሚታሰበው ወታደራዊው አምባገነን የደርግ ሥርዓት በተደመሰሰበት ወቅት ለሌላ ትግል የሚጋብዙ ፈታኝ የአስተሳሰብ ተግዳሮቶች በሀገሪቱ መፈጠራቸው አልቀረም፡፡ በወቅቱ ተራማጅ አስተሳሰብን የያዙ ፌዴራሊዝም ለዘመናት ደም አፍሳሽ የሆነውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ቀውስ ለመፍታት ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ያመኑ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በአንድ ጎራ ተሰለፉ፤፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ሁለት ፅንፍ ጫፍ ላይ የወጡ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ወገኖች ነበሩ።

በወቅቱ የታጠቁ ብሔር ተኮር ድርጅቶች መኖራቸው ቀዳሚው ጉዳይ ነበር፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ የችግሮቹ መፍትሄ መገንጣጠል ነው ብለው ያምኑም ነበር፡፡

በሌላኛው ወገን የሀገሪቱ መፍትሄ የሆነውን የፌዴራሊዝም ሥርዓት እንደ መበታተን አደጋ በመቁጠር ባረጀ እና ባፈጀ የአንድነት ስም የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ መብት ብሎም መፈቃቀድን “በእኛ እናውቅልሃለን” የፖለቲካ እሽክርክሪት በማጦዝ ሀገሪቱን ወደማያባራ ቀውስ ውስጥ ለመክተት አልመው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ነበሩ፡፡

ታዲያ በወቅቱ እነዚህን ተግዳሮቶች በሰከነ ብስለት በመፍታት ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊት ሀገርን ለመመስረት ከፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ከባድ ትግል ማካሄድ ግድ ብሎ ነበር፡፡ ውጤቱም በተራማጅ ኃይሎች አሸናፊነት እልባት አገኘ፡፡

ከዚህ በኋላም ቢሆን ሁሉም ነገር ቀላል አልነበረም። መግለፅ በሚያስቸግር መልኩ ሀገሪቱ ከባድ ፈተናዎች እንደገና ከፊት ለፊቷ ተደቀነባት፡፡ ከእነዚህ ፈተናዎች የላቀ ስፍራ የያዘው እና የሀገሪቱ ዋነኛ ጠላት የሆነው ድህነትን የመዋጋት ዘመቻ ነበር፡፡

ታዲያ ይህ የጋራ ጠላት መፍትሄ የሚያገኘው በመንግሥትና በመላ ሀገሪቱ ዜጎች የተባበረ ክንድ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍ በቅድሚያ መንግሥት የመሪነት ሚናውን በመውሰድ ህዝቡን በአስተሳሰብ ደረጃ በድህነት ላይ ድል እንዲቀዳጅ የማድረግ ኃላፊነትን በሚገባ ለመወጣት ቆርጦ ወደ ትግበራ ተገባ፡፡

በወቅቱም ድህነትን የመታገል ታላቅ ጉዞ እንዴት ሊከናወን ይችላል? ይህን የጋራ ጠላት ተዋግቶ ለማሸነፍ መሠረታዊ የሚባሉ ቁልፍ ጉዳዮችስ ምንድናቸው? የሚሉ ዐበይት ተግባራትን መለየት ወሣኝ ጉዳይ ነበር፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነውን ህገ መንግሥት ማፅደቅ ቁልፉ ተግባር ነው፡፡

ምንም እንኳን ህገ መንግሥቱን ለማፅደቅ መንግሥት መድረኩን ቢያመቻችም አንዳንድ የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂዎችና የህዝቡን የሥልጣን ባለቤትነቱን በአቋራጭ ለመንጠቅ ያሰፈሰፉ ፀረ ሠላም ኃይሎች ሁኔታውን በቀላሉ ሊቀበሉት አልፈቀዱም፡፡

ሆኖም በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግሥት ሥልጣን ከህዝብ የሚመነጭ መሆኑን እነዚህ ወገኖች በግልጽ እንዲያውቁ የተለያዩ ጥረቶችን ከማድረግ አልቦዘነም፡፡ እናም ሥልጣን የሚገኘው ከኢትዮጵያ ህዝብ በሚሰጥ ድምጽ እንደሆነም የማረጋገጥ ሰፊ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በዚህ ወቅት 'ሀገሪቱ ህገ መንግሥት ሊኖራት አይገባም እንዲሁም ብሔርን መሠረት ያደረገ ፌዴራላዊ ሥርዓት የምትገነባ ሀገር በምንም መልኩ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም' የሚሉ ተቃራኒ አመለካከቶች ዋነኛ ፈተናዎች ሆኑ፡፡

ታዲያ እነዚህ ጋሬጣዎች ዴሞክራሲያዊ ምላሽ እየተሰጣቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፈቅደውና ተማምነው ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ህገ መንግሥትን አፀደቁ፡፡ ይህ ህገ መንግሥትም የቃል ኪዳናቸው ሰነድ በመሆን የኢትዮጵያ ህዝቦችን የዘመናት ጥያቄዎች ሊመልስ በቃ፡፡

ሀገርን አዋርዶና ህዝብን አሸማቅቆ ዜጎችን ለተመፅዋችነት የዳረገው ብሎም ለዘመናት ከጫንቃቸው ላይ አልወርድ ብሎ ከኖረውና ድህነት ከተሰኘው ክፉ ጠላት ጋር ግልፅ ውጊያ መግጠም ተያዘ፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ከድህነት በላይ ጠላት እንደሌላቸውም አረጋገጡ፡፡ ይህን በጽናት ለመዋጋትም እጅ ለእጅ ተያያዙ፡፡

ዜጎች በመንግሥት በተነደፉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመሩ በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ዕድገት ማስመዝገብ ጀመሩ። ከድህነት አዙሪት ተላቀው ወደ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት መሸጋገርን ተያያዙ፡፡ ውጤቱንም ማጣጣም ጀመሩ፡፡ ህገ መንግሥቱ ፀድቆ በሀገሪቱ የፌዴራል ሥርዓት እውን ከሆነ ወዲህ የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ምላሽ እያገኙ መጡ፡፡

ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ የሚፈልጉትን ኃይማኖት የመከተል፣ በቋንቋቸው የመናገር እና የመጻፍ፣ ባህላቸውን እና እሴቶቻቸውን በነጻነት የመግለፅ መብቶቻቸን ህገ መንግሥቱ በማያሻማ መልኩ አረጋገጠላቸው፡፡ በእርግጥም የኢትዮጵያ ህዝቦች የዘመናት ትግል መንስዔም እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ነበርና ነበርና ይህም ሆነ፡፡

ጨለምተኞች የፌዴራሊዝም ሥርዓት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ከሆነ ሀገሪቱ ወደማያባራ ጦርነት ውስጥ ትገባለች፤ ሀገሪቱም የመበታተን አደጋ ይገጥማታል፣ ህዝቦቿም በየጎራው ተከፋፍለው እርስ በርሳቸው ይጨራረሳሉ በማለት አሟረቱ፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ መገናኛ ብዙኃን ብዙ ደሰኮሩ፤ የፖለቲካ ተንታኞች ብዙ ቀበጣጠሩ፤ ጽንፈኞች ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ለሀገሪቱ አይበጅም ሲሉ ብዙ አራገቡ፡፡

እነዚህ የመገናኛ ብዙኃንና ጨለምተኞቹ በሀገሪቱ የተዘረጋው ፌዴራላዊ ሥርዓት ህዝቦችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ጠፍቷቸው አልነበረም፤ ይልቁንም የቀድሞው ሥርዓት ናፋቂ ከሆኑት ፅንፈኛ ኃይሎች ጋር በመሰለፍ ማቀንቀኑን መርጠው እንጂ፡፡

ጨለምተኞቹና ጽንፈኞቹ ያሻቸውን ቢሉም መንግሥትና ህዝቡ በውዥንብራቸው ሳይዘናጉ ብዝኃነታቸውን ውበታቸው በማድረግ አንድነታቸውን አጠናክረው ለጋራ ዕድገት መረባረቡን መረጡ፡፡

የፌዴራሊዝም ሥርዓት በማህበራዊ ምንነት ምክንያት የሚፈጠር ልዩነቶችን ለማቻቻል አብሮ ለመጓዝ ብሎም በማህበራዊ ምንነት ወይም በሌላ የማንነት ልዩነቶችን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን ለማስተንፈስ አግባብነት ያለው የፖለቲካ መሣሪያ መሆኑን የመስኩ ተመራማሪዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህ አብሮነትም ዜጎች የጋራ ምጣኔ ሀብታቸውን ለማሳደግ ሥርዓቱ የጎላ ሚና እንደሚጫወትም እምነት ተይዟል፡፡

ይህን እውነታ የተገነዘበው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊው የሀገሪቱ መንግሥትም ህገ መንግሥቱን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው ተስማምተው እና ተማምነው እንዲያፀድቁት የተጫውተው ሚና የላቀ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ከአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት አገዛዝ ያላቀቀው ኢህአዴግ መራሹ ሥልጣን በህዝብ እና በህዝብ ብቻ የሚረጋገጥ እንደሆነ በማመን ዜጎች የትግላቸው ባለቤት እንዲሆኑ አስችሏል፡፡

ህገ መንግሥቱ የህዝቦች የዘመናት ትግል ውጤት ነውና፤ ይህን የህዝቦችን የዘመናት ትግል ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር ህገ መንግሥቱም ሊረቀቅና ሥራ ላይ ሊውል የቻለው፡፡

የኢትዮጵያ ባህል፡ ቋንቋ እና ታሪክ ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህሎች፡ ቋንቋዎች እና ታሪኮች ተደምረው የሚፈጥሩት ነው፡፡ ይህ እውነታ በልዩነት የሚስተናገደው በፌዴራሊዝም ሥርዓት ነው፡፡ እናም ለሀገሪቱ ብቸኛው አማራጭ ፌዴራላዊ ሥርዓትን መከተል እንደሆነም አማራጭ የለውም፡፡

አንዳንድ ጨለምተኞችና ፅንፈኞች ሀገሪቱ ባልተረጋጋ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግር ትናጋለች፣ ህዝቦቿም እርስ በርሳቸው ይተላለቃሉ የሚሉ አሳቤዎችን ከተቃዋሚ ኃይሎች የእብደት ትንታኔ እየሰጡ ዋትተዋል፡፡ ሆኖም ይህን የሴራ አቋማቸውን ማንም አልተጋራቸውም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡

የፌዴራል ሥርዓቱ ጨለምተኞቹ የሚሉትን ዓይነት በድንቡሽት የተገነባ ቤት ሳይሆን፤ በህዝቦች ፈቃድ ተረጋግጦ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ በመሆኑ ነው። እናም

ሥርዓቱን የተመለከቱበት መነፅር የተሳሳተና የተገለበጠ ህልም ብቻ የሚያሳያቸው መሆኑ በተግባር ታይቷል፡፡

እነዚህ ጨለምተኞችና ጽንፈኞች የታላቁ መሪያችን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ የዜና ዕረፍት ተከትሎ ያልቀባጠሩት አሉባልታና የወሬ ዓይነት አልነበረም፡፡

የእነርሱ የወሬ ማራገቢያ የሆኑት ሚዲያዎችን በመጠቀምም ‘ኢትዮጵያ ከድህረ መለስ በኋላ የተረጋጋ መንግሥት አይኖራትም’ የሚል ትንቢት መሳይ ቅጥፈትን ማስታወስ በቂ ይሆናል፡፡ በእርግጥ እነዚህ ሟርተኞች ይጠቅመናል ብለው ካሰቡ ምንም ነገር ከማለት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም፡፡ አሁን ከድህረ መለስ በኋላ እነርሱ የተመኟት ኢትዮጵያ ‘አለች ወይ?’ ብለው እንኳን የማይጠይቁ ባዶ ሰማይ ቧጣጪ ተስፈኞች ናቸው።

እርግጥ ነው! የእነርሱ በከሰረ የፖለቲካ እሳቤያቸው የሚያራምዱት ‘የሀገር ትበታተናለች’ የተሳሳተና መነሻና መድረሻ የሌለው ትንታኔ ከእነሱ ውጪ ማንንም ሊያሳምን አይችልም፡፡ ማንም ጤናማ አዕምሮ ያለው የሰው ፍጡር እንደሚገነዘበው ያኔ በክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ ሞት ያልተደናገጠ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ አልነበረም፡፡

ህዝቡ ለመሪው የነበረውን ጥልቅ ፍቅር አስከሬናቸው ከውጭ ሀገር በመጣበት ወቅት ፀሐይ፣ ዝናብ እና ብርድ ሳይበግረው አስመስክሯል፡፡ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘኑንም እንዲሁ ገልጿል፡፡ ፅንፈኞቹ ግን ይህን አይተው ሲያበቁ መለስን የሚተኩ እልፍ አዕላፍ መለሶች እንዳልተፈጠሩ ሁሉ ሀገሪቱ አበቃላት ሲሉ ቢሳለቁም ህዝቡ ግን ጆሮውን ሊያውሳቸው አልፈቀደም፡፡ አንድ እውነታ አለ፡፡ የክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ - ህይወት ጥልቅ ሀዘንን እና ድንጋጤን መፍጠሩ ሀቅ ነው፡፡

ህዝቡም ከጫፍ እስከ ጫፍ ተነሳስቶ ታላቁ መሪያችን በቀየስክልን ፌዴራላዊ ሥርዓት መርህን አንግበን አንድነታችንን በማጠናከር በእልህ እና በወኔ ራዕይህን እናሳካለን ብሎ ቃል መግባቱም ሌላው እውነታ ነው፡፡ የውጭ መገናኛ ብዙኃንም ከጨለምተኞቹና ከፅንፈኞቹ በተፃራሪ ህዝቡ ለመሪው ያለውን ፍቅር የገለጸበትን

መንገድ በማድነቅ ‘መላ ኢትዮጵያዊያን የሚወዱትን መሪያቸውን በክብር ሸኙ’ ሲሉ ዘግበዋል፡፡

የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንዲህ ሲሉ የሀገሬ አንዳንድ ተቃዋሚዎችና ፅንፈኛ ኃይሎች ግን የገዛ ሀገራቸው ለብተና ትዳረጋለች ብለው ማሚረታቸው አስገራሚም አስደናቂም ነበር፡፡ በዚሁ ድርጊታቸው በህዝቡ ዘንድ ትዝብትን እንጂ ያተረፉት ነገር የላቸውም። ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው የፌዴራላዊ ሥርዓቱን ጥንካሬ ብሎም የህዝቦችን አንድነት በማጠናከሩ ረገድ የላቀ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው፡፡ ህገ መንግሥቱን በጽናት ለመጠበቅ ቃል ተገባብተዋል፡፡

ታዲያ ከትናንቱ ማንነታቸው ያልተማሩት ተቃዋሚ ተብዬዎችና ፅንፈኛ ኃይሎች ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ አይተው እንዳላዩ መሆንን መርጠዋል፡፡ ይልቁንም ዛሬም ሥርዓቱን በባዶ ሜዳ ላይ ያለ አንዳች ተጨባጭ አስረጅ እንዲሁም በማኅበረሰቦች ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን ጊዜያዊና ነባራዊ ሁነት በማጦዝ ከማጥላላት አልቦዘኑም።

ታዲያ ይህ እኩይ ተግባራቸውም የሚያመላክተው ነገር፤ ልክ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ታሪክ ራሱን በመድገም እነዚህ ኃይሎች የሥርዓቱን እመርታ ቁጭት በተንሸዋረረው የተገለበጠ መነፅር እየተመለከቱ ለማደናገር መሞከራቸውን ነው።

እርግጥ የማምታታትና የማደናገር ሙከራቸው ምንም ውጤት ሊያስገኝላቸው አልቻለም፡፡ መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በደማቸው የፃፉት ህገ መንግሥት ፀድቆ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችም በአንድነት ተሳስረው የእድገት ጉዟቸውን ተያይዘውታል፡፡

አላዛኞችም የሚደልቁት የቁርጦ ቀጥልነት አታሞም ሰሚ አጥቷል፡፡ እናም በሚያስገርም ጨለምተኛ እሳቤያቸው ዓለም የመሰከረውንና ዕድገት ያመጣውን ፌዴራላዊ ሥርዓት ከሽፏል ይሉናል፡፡

አንዳንዶቹ ጭራሹኑ በግጦሽ ቦታና በውኃ ምክንያት በአንዳንድ የሀገራችን ብሔረሰቦች መካከል ለዘመናት ሲከሰቱ የኖሩ ግጭቶች መኖራቸውን እንዲሁም አማርኛ

ተናጋሪዎች ከአንዳንድ አካባቢዎች ተባረሩ በሚሉ  የፌዴራል ሥርዓቱ በእነዚህ ጉዳዮች ምክንያት ከሽፏል ብለው ይሉናል፡፡ በድፍረትም ፅፈዋል።

በጨለማ ውስጥ ሆነው በገሀዱ ዓለም የሌለን ነባራዊ ሁኔታ እየተነተኑ አፈ ታሪክ ያንበለብሉልናል፡፡ በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ግጭት መቼም ቢሆን ሊጠፋ የማይችል ነባራዊ ሁኔታ መሆኑን እያወቁም ወይም ቢያውቁም ለመናገር የሚደፍሩ አይደሉም። ምክንያቱም ለእነርሱ ጥላሸት የመቀባት ሥራ ይህ ሀቅ ምንም ስለማይጠቅማቸው ነው።

ሆኖም እንኳንስ የህዝቦች ንቃተ ህሊና እየተገነባ እና ይበል የሚያሰኝ ደረጃ ላይ እየደረሰ ባለበት በእኛ ሀገር ውስጥ ቀርቶ በሥልጣኔ በበለፀጉ ሌሎች ሀገሮች ውስጥም ቢሆን ግጭት መኖሩ አይቀርም። ምን ይህ ብቻ፡፡ ሰው ከራሱ፣ በአቅራቢያው ካለውና ከተፈጥሮ ጋር መጋጨቱም አይቀሬ ነው።

ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዓለማችን ላይ ያለው የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየች አይደለችም – እንደ ማንኛውም የዓለማችን ክፍል የተፈጥሮ ሀብት እጥረት አለባት። እናም ግጭት ትናንትም ይሁን ዛሬ መኖሩ ያለና የሚኖር ጉዳይ ነው።

ሆኖም ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ካለፉት ጊዜያት ጋር ፈፅሞ በማይገናኝ መልኩ ለዚህ ነባራዊ ችግር ትኩረት ሰጥቶ በመስራቱ ሁኔታውን በመለወጥ ላይ ይገኛል። የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ እንዲጠቀሙና ከሌሎች ህዝቦች ጋር በመተሳሰብ የጋራ ሀብታቸው እንዲሆን ማድረግ ችሏል።

ዳሩ ግን ያለፉት ሥርዓቶች በሀገሪቱ ህዝቦች ውስጥ ፈጥረውት ያለፉት የተዛቡ አመለካከቶች እንዲሁ በቀላሉ በጥቂት ዓመታት በቀላሉ የሚቀየሩ አይደሉም – ሂደትን፣ ጊዜንና የአስተሳሰብ ለውጥን ይጠይቃሉ። አንዳንዶች ይህን እውነታ ወደ ጎን ገሸሽ አድርገው ሥርዓቱን ጥላሸት ለመቀባት ካላቸው ፍላጎት ብቻ በመነሳት 'የከሸፈ ፌዴራሊዝም' መሆኑን ያለ አንዳች ሐፍረት ሊነግሩን ሞክረዋል።

እንደ ሟርተኞቹ እሳቤ ሳይሆን የፌዴራል ሥርዓቱ በእርግጥም አልከሸፈም። ይልቁንም ሥርዓቱ የሀገሪቱን ህዝቦች በአንድነት በማስተሳሰር ከሰሃራ በታች ጠንካራ ምጣኔ ሃብት

መገንባት የቻለና ህዝቡንም በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ሆኗል። ስለሆነም 'የክሽፈት ዓለም' ምኞት በጨለምተኞቹና በጽንፈኞቹ ምናብ ውስጥ እንጂ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የሌለ መሆኑን ማሳወቅ ተገቢ ይሆናል።

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ይልቅ ባህር ማዶ ባሉና የራሳቸው እኩይ አጀንዳ ባነገቡ ግለሰቦች አባባሎች የሚያምኑና እነዚያን ሽውራራ ዕይታዎች እንደወረዱ የሚያቀርቡ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ስለፌዴራል ሥርዓቱ ክሽፈት ሊናገሩ ሲቃጣቸው ከእውነታው በአያሌው ማፈንገጣቸውን ይዘነጉታል፡፡

አንድ መታወቅ ያለበት እውነታ አለ፡፡ ኃላፊነት በማይሰማቸው ግለሰቦች አማካይነት ተፈናቅለው የነቡትና ኋላ ላይም በመንግሥት ውሳኔ ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ የተደረጉት ወገኖች አማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ አይደሉም። የኦሮሚኛና የሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎችም ይገኙበታል። የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ብቻ እውነታውን በመገልበጥ ህዝቦችን ከህዝቦች ጋር ለማጋጨት መሞከር አሳፋሪም አሳዛኝም ነው፡፡

እንዲህም ተባለ ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተገነባ ያለው ሥርዓት ራሱን በራሱ እያረመና እያስተካከለ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። እንደሚታወቀው ማንኛውም ፌዴራላዊ ሥርዓት በአንድ ጀምበር የተገነባ አይደለም።

ተግዳሮቶች መኖራቸው አይቀርም። እናም በሂደቱ ውስጥ ጥቃቅን ስንክሳሮች ሊያጋጥሙት ይችላል። ዋናው ነገር እነዚህ ጊዜያዊ ችግሮች በብቃት እየተፈቱ የመሄዳቸው ጉዳይ ነው።

ከዚህ አኳያ በሀገራችን በመገንባት ላይ ያለው ፌዴራላዊ ሥርዓት ለሚፈጠሩ ሁነቶች ወቅታዊና አስተማማኝ ምላሽ እየሰጠ ዛሬ ላይ የደረሰ መሆኑ ነው። በዚህም ሊፈጠሩ የሚችሉ አነስተኛ ኑባሬያዊ ተግዳሮቶችን በመፍታት ሁሉም የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተሳስበውና ተፈቃቅደው የሚኖሩበትን አስተማማኝ ሥርዓት መፍጠር ተችሏል።

ከዚህ ውጪ አንዳንዶች በጨለምተኛ እሳቤያቸው እንደለመዱት 'እነ እገሌ እንዲህ ስለሆኑ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ከሽፏል' ማለታቸው የሚያነሱት ሀሳብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ከማሳበቅ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም።

ሁኔታው አስገራሚም አስቂኝም ነው። መቼም ጭልጥ ባለ የጥላቻ መዘውር እየተመራ በእውር ድንብሩ የሚያስብ  የሚበላውን ዳቦ ድንጋይ ነው ቢል የሚፈረድበት አይደለም – ማንኛውንም ነገር ከመካድ ወደ ኋላ የሚሉ አይደለምና።

ግራ ተጋብተው ሌሎችን ግራ ለማጋባት የሚውተረተሩ ጥቂር ቀለም ቀቢዎች ሸውራራ ሀሳብ ጠቅለል ተብሎ ሲታይ፤ ገዥው ፓርቲ የብሔር ብሔረሰቦችን ሉዓላዊ መብት ለፖለቲካ ፍጆታ እየተጠቀመበት እንደሆነ በተለመደው 'እገሌ የተባለ ሰው እንዲህ ስላለ ትክክል ነው' በሚል ጉንጭ አልፋ ክርክር ሊሞግቱ ይዳዳቸዋል፡፡

ይህን የለየለት ውሸት በሚገባ ለሚገነዘብ በጉዳዩ ላይ ብዙ ማለት ተገቢ አይደለም። ይሁንና እዚህ ላይ አንድ ሀቅን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ገዥው ፓርቲ የታገለለትንና በህገ መንግሥቱ ውስጥ ተካትቶ ዛሬም ሆነ ነገ በፅናት የሚያምንበትን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የማይገሰሱ መብቶች ላይ ከቶም ቢሆን ድርድር እንደማያውቅ ነው።

ጨለምተኞችና ቢጤዎቻቸው እንደሚያስወሩት ሳይሆን፤ የብሔረሰቦች መብት አያሌ የሀገራችን ህዝቦች ውድ ልጆች ቤዛ የሆኑለትና ለተግባራዊነቱ ህዝቦች በሙሉ የተረባረቡበት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ገዥው ፓርቲም ይሁን የሀገራችን ህዝቦች ያላቸው አቋም መቼም ቢሆን ሊቀለበስ የሚችል አይደለም። እናም አሉባልታ ነዥዎች ሲያምራቸው ይቀራታል እንጂ ያሰቡት አይሆንም፡፡

ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በህልም ዓለም ቅዠት ሲያፈርሱ የሚያድሩት የሀገራችንና የህዝቦቿ ጠላቶች፣ አሸባሪዎችና ፀረ ሠላም ኃይሎች እንጂ፤ በህገ መንግሥቱ ያገኘውን መብት ተጠቅሞ በሠላማዊ ሁኔታ ሥራውን የሚያከናውን ዜጋ አይደለም፡፡

ፀረ ሠላምና ፀረ ልማት የውስጥና የውጭ ኃይሎች እንደሚመኙት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተስማምተው ያፀደቁትና የሉዓላዊ ሥልጣናቸው ምንጭ የሆነው ህገ መንግሥት እነዚሁ ህዝቦች እስካሉ ድረስ ፈራሽ የሚሆንበት ምንም ዓይነት ዕድል የለም፡፡

የህዝቦችን ሉዓላዊ መብት በህልምም ቢሆን ለመጋፋት መሞከር ትርፉ ከህገ መንግሥቱና ከባለቤቶቹ ጋር በይፋ መላተም መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ውጤቱም ፈራሽ ሀሳብን በምድረ በዳ ላይ አቀንቅኖ ተተፍቶ መጣልን ያስከትላልና፡፡

ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በሂደት ራሱን በራሱ እያረመ ለዛሬው የህዝቦች መፈቃቀድና አንድነት ያበቃን ብሎም ከመበታተን ይልቅ በዕድገት ማማ ላይ እንድንወጣና ባለ ድል እንድንሆን ያደረገን ነው፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን አብሮነት በመሸርሸርና በጨለምተኝነት መሐረብ ተጀቡኖ በቁጭት ማላዘን ዛሬ ጊዜው አልፎበታል፡፡

ትናንት ዛሬ አይደለም። ሥርዓቱ ራሱን እያረመና እንደ ማንኛውም የፌዴራል ስርዓት ጀማሪ ያሉበትን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ይገኛል። በአሉባልታም የሚፈታ አይደለም።

ህዝቦች ይህን ስርዓት ለማምጣት ያልከፈሉት የአካልና የህይወት መስዕዋትነት የለም፡፡ እናም ለቁራ ጩኸት ባለሟሎች የሚሰጡት ጆሮ ሊኖር አይችልም። ለምን ቢሉ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዛሬ የውርደት ሸማ ያከናነባቸውን ድህነት በስራ ለመርታት ከምንግዜውም በላይ ደፋ ቀና በማለት ላይ በመሆናቸው ነው።

ስለሆነም አንድ ክስተት ኮሽ ባለ ቁጥር ፌዴራላዊ ሥርዓቱን በል ሲላቸው 'አንድነትን ያጠናክርም'፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ 'ገዥው ፓርቲ የሚከተለው የብሔር ፖለቲካ ችግር እየፈጠረ ነው' የሚሉና ከነባራዊው ዕውነታ ጋር የማይገናኙ ዕውቀት አጠር ዲስኩሮች በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት የለውም።

ዓላማውም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሶችና ህዝቦች በመራር ተጋድሎአቸው ያገኙትን ህገ-መንግስታዊ መብት ሆን ብሎ ለመሸርሸር የታለመ በመሆኑ ሰሚ የለውም። እናም የህዝቦችን ህገ-መንግስታዊ መብት በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ማጣጣል ስለማይቻል እነዚህ ወገኖች ሊያተርፉት የሚችሉት ምንዳ የሌለ መሆኑን ማወቅ አለባቸው—ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የዜጎችን ተቻችሎ የመኖር መንፈስ አጠናክሯልና።